# ብአዴን ለአማራው የመጣለት ወይስ የመጣበት

## ከቻሌ ተሾመ

የአማራውን ክልል በመምራት ላይ የሚገኘው ብአዴን የተባለ የህወኃት ጥላ ድርጅት የተመሰረተበትን 30ኛ ዓመት በተመለከተ በዋሽንግተን ዲሲ በሞቀበት የሚዘፍኑ ሚዲያዎች ማስተገባትን ይዘዋል፡፡፡ በተለይ በዚሁ ድርጅት ቀድሞ ታጋይ ነበርን የሚሉ የትግል ውሉና ጉዞው የጠፋባቸው ተጋባዦች የሰጡትን አስተያየት በተመለከተ አቶ ተድላ አስፋው «Ethiopian Movement Vs Amahara national» በሚለው የእንግሊዝኛ መጣጥፋቸው በመዳስስ ከኢትዮጵያዊ ስም ወደ ክልላዊ ሰያሜ የተቀየረበትን ምክኒያት በትክክል አስቀምጠውታል ብየ አስባለሁ፡፡

ብአዴን (ኢህዴን) በታገለባቸው የአማራ አካባቢዎች ዓላማውን ያልደገፉትን በማሰር፣ በመግደል፣በማሳደድ የሚታወቅ ሲሆን፣በተለይ በአማራው ክልል  የተሻለ መሬትና ሀብት ያላቸውን « ፊውዳል » በማለት ሀብታቸውን በመውረስ ድህነትን በክልሉ በስፋት ያከፋፈለ ድርጅት ነው፡፡

ኢህዴን  ብአዴን ከመሆኑ በፊት የአማራ ለም መሬቶች በተለይ በጎንደርና በወሎ ለትግራይ ተከልለው እንዲሰጡ በርትቶ ሰርቷል፡፡ የወልቃይት፣ሁመራ፣ጠገዴ ሰፋፊ መሬቶች በራሱ በኢህዴንና በህወኃት አባላት አማካኝነት ከቀበሌ ቀበሌ በማካለል ለትግራይ ገፀ በረከት በማቅረብ የሚታወቅ ድርጅት ነው፡፡የጎንደርና የወሎ አካባቢዎች ያላአግባብ መከለሉን አስመልክቶ የተቃወሙ ግለሰቦችንና  የአገር ሽማግሌዎች እስትንፋሳቸው እንዲጠፋ ከማድረጉም በላይ የተለመደው የስድብና የአስፀያፊ ስያሜዎች ሰለባ በማድረግ አሽማቅቋቸዋል፡፡

ኢህዴን እ.ኢ.አ በ1986 በድንገት  ተነስቶ ብአዴን ነኝ በማለት የአማራውን ህዝብ በብቸኝነት ለመመዝበርና ለማስመዝበር በወያኔ  የተፈለሰፈ የመጨቆኛ መረብ ነው፡፡

ብአዴን በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የአማራ ተወላጆች በወቅቱ በተነሱ ጠባቦች ጅምላ ጭፍጨፋ ሲካሄድባቸው እንዳላየ ሆኖ «ለነፍጠኛው» ዋጋው ነው በማለት ለአማራ ህዝብ ያለውን ግልፅ ጠላትነት ያረጋገጠ ድርጅት ነው።

በምስራቅ ወለጋ የዕለት ጉርስ ፍለጋ የሰፈሩ የአማራ አርሶ አደሮች በአዲሶቹ የወያኔ ባለሟሎች ጅምላ ጭፍጨፋና ማፈናቀል ሲፈፀም አበጃችሁ ብሎ በደረሰው ጉዳት ላይ የሚያባብስ በደል ከመፈፀሙም በላይ፣ አማራው በሌላ ብሄር ክልል መስፈርና መስራት የለበትም ብሎ አማራው ራሱን ችሎ በኢትዮጵያ አገሩ የትም ሰርቶ የመኖሩን ነፃነት የተቃወመ የአማራ ህዝብ ጠላት ድርጅት ነው።

ብአዴን በምዕራብ አማራ ክልል ያለው የተፈጥሮ ሀብት «ሰፈራ» በሚል ጥናት የጎደለው ዘመቻ እንዲመናመን በማደረግ የአማራው ክልል ይበልጥ እንዲራቆት አልሞ የሚሰራ የተፈጥሮ ሀብት ጠላት ነው።

ይህ ድርጅት በአማራው ህዝብ ላይ ከፍተኛ ንቀት ያለው ከመሆኑም በላይ የአማራው ህዝብ ገዢ የነበረ የህ/ሰብ ክፍል ነው ብሎ ሰድቦ ለሰዳቢ በመስጠትና ከሌሎች ህዝቦች ጋር በማጣላት አማራው በገዛ አገሩ አንገቱን ደፍቶና አፍሮ እንዲኖር የሚያደርግ ድርጅት ነው።

ብአዴን በአማራው አካባቢ የራሱ ሰዎች እያሉ ከሌላ አካባቢ የሚመጡ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንዲበልፅጉ እንዲከበሩ የሚሰራ የአማራው ክልል ግን በድህነትና በስደት እንዲሰቃይ የሚያደርግ ድርጅት ነው።

በአጠቃላይ ብአዴን ለአማራወ ህዝብ ሊደገፈው የመጣ ሳይሆን ሊያዋርደው፣ሊያደኸውና ሊያሰድደው የመጣበት ጠላት ነው።የአማራው ክልል ተገዶ የ30ኛ አመት የውርደት በዓሉን ሊያከብር እንዲችል አድርባይ የአማራ ልጆች ሰሞኑን ተግተው በመስራት ላይ ናቸው።

For your comment sportyb4321@yahoo.com